# በደብረ ሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቤዛ-ኵሉ ሰንበት ትምህርት ቤት ትምህርት ክፍል ሚኒያፖሊስ ሚኒሶታ ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል የተዘጋጀ ትምህርት።

# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

# ልደተ ክርስቶስ

የነቢያት ትንቢት ፍጻሜ አግኝቶ አምላካችን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ የተወለደበትን የምሕረት ቀን ከማየታችን በፊት በዚህ በታኅሣሥ ወር ያለፉትን አበይት በዓላት በመጠኑ እንዳስሳለን።

**ብርሃን፡-** ከታኅሣሥ ፲፬-፳ በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ይህ ጊዜ ብርሃን በመባል ይታወቃል። ነቢያት ስለ ጌታ በተናገሩት ትንቢት ብርሃንነቱን አምልተውና አስፍተው ጽፈዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ስለመሆኑ ከመናገሩ በፊት በነቢዩ በኢሳይያስ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፏል፡-

- እኔ እግዚአብሔር በጽድቅ ጠርቼሃለሁ፥ እጅህንም እይዛለሁ እጠብቅህማለሁ፥ የዕውሩንም ዓይን ትከፍት ዘንድ የተጋዘውንም ከግዞት ቤት በጨለማም የተቀመጡትን ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ ለሕዝብ ቃል ኪዳን ለአሕዛብም ብርሃን አድርጌ እሰጥሃለሁ። ኢሣ.፵፪፡፮-፯

ወንጌላዊው ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃንነት በገለጸበት ምዕራፉ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስን በመጥቀስ መጥምቁ ስለ አምላካችንና ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃንነት ሊመሰክር መጣ እንጂ እርሱ ብርሃን አልነበረም በማለት የኢየሱስ ክርስቶስን አማናዊ ብርሃንነት በገሐድ መስክሯል። ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም መጥቷልና። በነቢያት ትንቢት የተነገረለትና የንስሐ ጥምቀት እያጠመቀ ብዙዎችን በታላቅ ትምህርቱ ወደ እርሱ መሳብ የቻለው መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ የተጠራበትን ነገር ጠንቅቆ ያውቅ ስለነበረና በተጠራበትም መስክ ታማኝ ስለነበር ብርሃን ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመሰክር እንዲህ ብሎናል፡-

- ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው፤ ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድምጽ እጅግ ደስ ይለዋል። እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ። እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል። ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤ ከምድር የሚሆነው የምድር ነው የምድሩንም ይናገራል። ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው። ዮሐ.፫፡፳፱-፴፩

ጌታችንም ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው በማለት በመጥምቁ ዮሐንስ የተነገረውን ቃልና ስለ ብርሃንነቱ የተመሰከረለትን ምስክርነት ሲያጸናው እናንተ ከታች ናችሁ፥ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፥ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም። (ዮሐ.፰፡፳፫) እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም። ዮሐ.፰፡፲፪ በማለት ተናግሯል። በመሆኑም ብርሃን ተብሎ ይኽ ዕለት የሚታሰበው የጌታችንን ብርሃንነት አምልቶና አስፍቶ ለማስተማር ነው።

**ኖላዊ፡-** ከታኅሣሥ ፳፩-፳፯ በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ይህ ጊዜ ኖላዊ በመባል ይታወቃል። ኖላዊ መሰኘቱም እግዚአብሔር እንዴት ባለ ሁኔታ ልጆቹን እንደ እረኛ መንከባከቡን ለመግለጽ ሲሆን በዚሁ አጋጣሚም የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲጠብቁ ሥልጣን የተሰጣቸው እረኞች እረኝነታቸውን በአግባቡ እንዳልተወጡት ለመግለጽ ነው። በመሆኑም በብሉይ ኪዳን ከተነገረው የትንቢት ቃል እንዲህ የሚለውን ቃል እናገኛለን፡-

- ... ራሳቸውን ለሚያሰማሩ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው! እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን?...የደከመውን አላጸናችሁትም የታመመውንም አላከማችሁትም የተሰበረውንም አልጠገናችሁትም የባዘነውንም አልመለሳችሁትም የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም በኃይልና በጭቈናም ገዛችኋቸው። እረኛንም በማጣት ተበተኑ፥ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ፥ ተበተኑም። ...በጎቼም በምድር ፊት ሁሉ ላይ ተበትነዋል፤

የሚሻም የሚፈልግም አልነበረም። ...እነሆ፥ እኔ ራሴ በጎቼን እሻለሁ እፈልግማለሁ። ...የባዘነውንም እመልሳለሁ የተሰበረውንም እጠግናለሁ የደከመውንም አጸናለሁ፤ የወፈረውንና የበረታውንም አጠፋለሁ፤ በፍርድም እጠብቃቸዋለሁ። ሕዝ. ፴፬፡፮-፲፮

ይኽ በነቢዩ ሕዝቅኤል ላይ የተነገረው ቃል በሐዲስ ኪዳን የበለጠ ተፈጻሚነትን አግኝቶ የተበተኑት ይሰበሰቡ ዘንድ ታማኝ እረኛ ስለማስፈለጉ አምላካችን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጎቹን ለመጠበቅ ቸል እንደሚሉት ዓይነት እረኞች ሳይሆን ለጠፋት በጎች ስለሚገደው፡-

- መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል። እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኵላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኵላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል። ...መልካም እረኛ እኔ ነኝ፥ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ። ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምፄንም ይሰማሉ፥ አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ። ዮሐ.፲፡፲፩-፲፮

በማለት ያስተምረናል። በመሆኑም ኖላዊ በመባል የሚታወቀው ይኽ ጊዜ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም እረኝነት ይሰበከበታል፤ ይነገርበታል።

# ልደተ ክርስቶስ

ዓመተ ፍዳና ዓመተ ኵነኔ በመባል የሚታወቀው የጥፋት ዘመን የተሻረበትና በነቢዩ በኢሳይያስ ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ኢሣ.፱፡፮ ተብሎ የተነገረው የትንቢት ቃል ፍጻሜን አግኝቶ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ይኽ ቀን የባርነት ሰንሰለት የተፈታበትና ዓመተ ምሕረት ተብሎ የተነገረበትም ታላቅ ወቅት ነው። በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ብርሃንን ያየበት ይኽ ቀን ልዩና ድንቅ በመሆኑ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡-

- እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ፥ በመንፈስ የጸደቀ፥ ለመላእክት የታየ፥ በአሕዛብ የተሰበከ፥ በዓለም የታመነ፥ በክብር ያረገ።

በማለት ይኽን ታላቅ ምሥጢር በታላቅ መገረም በጢሞቴዎስ መልእክቱ ምዕራፍ ፫፡፲፮ ላይ አስፍሮታል። የማይወሰነው ተወስኖና በታላቅ ትሕትና የባሪያን መልክ ይዞ ወደ ምድር የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ የዲያብሎስን ሥራ ሊያፈርስና የጠፋውን ሊፈልግ ነው።

# ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ የነበሩ ሁኔታዎች፡-

ሰብዓ ሰገል ኮከቡን በምሥራቅ አይተው ወደ ኢየሩሳሌም መምጣታቸውን ንጉሡ ሄሮድስ በሰማ ጊዜ እንደ ጀምበር ለሚጠልቅና ታይቶ ለሚጠፋ ሥልጣን ተጨንቆ ዓለምን ለማዳን የመጣውን ጌታ የምድር ሥልጣኑን ሊወስድበት እንደሆነ በመገመት ከካህናት አለቆች ከጻፎች ስለ ሁኔታው ለማወቅ ጌታ የት እንደሚወለድ ይጠይቅ ጀመር። እነርሱም በነቢያት የተጻፈውን ትንቢት እንዲህ እንደሚል ነገሩት፡-

- አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል። ሚክ. ፭፡፪

ሄሮድስ ይኽን ቃል ሲሰማ እጅግ በመደናገጡና የኢየሱስ ክርስቶስም መወለድ ለሥልጣኑ እንደሚያሳስበው በመገመት ሰብዓ ሰገልን በስውር ጠርቶ ሕፃኑን ባገኛችሁት ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ በማለት በሐሰት የተቀመመና በሬት የተለወሰ እውነት የሚመስል ከንቱ አነጋገርን ተናገራቸው። ሰብዓ ሰገል ጌታ በኢየሩሳሌም እንደሚወለድ እንጂ በየት ሥፍራ እንደሚወለድ አያውቁም ነበር። ሆኖም ግን በምሥራቅ ያዩት ኮከብ እየመራ ጌታችን እስከተወለደበት ስፍራ ድረስ አድርሷቸው ቆመ። ዓለም ዛሬ በደረሰበት ሥልጣኔ ከቦታ ወደ ቦታ ለመዘዋወር ጂፒኤስ በመባል መሣሪያ ሲንቀሳቀስና ወዳሰበበት ቦታ ያለ ችግር መድረሱ ገሐድ የሆነለት በቅርብ ጊዜ ሲሆን ሰብዓ ሰገል ግን በእግዚአብሔር ፍቃድ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ኮከብ እየመራቸው ጌታ የተወለደበት ስፍራ አድርሷቸዋል። ከሁሉ

የሚገርመው ደግሞ ሰብዓ ሰገል የሄሮድስን ትእዛዝ ሰምተው ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይመለሱ ሦስቱም አንድ ዓይነት ኅልም ማየታቸው ነው። በኮከብ እየተመሩ ጌታ ከተወለደበት የደረሱት የጥበብ ሰዎች በሕልም ተነግሯቸው ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ወደ መጡበት ስፍራ ተመልሰዋል። ለሰብዓ ሰገል በኅልም አቅጣጫን ያመላከታቸው እግዚአብሔር ለዮሴፍም የጌታ መልአክ በኅልም ታይቶ እንዲህ ሲል መልእክትን ነገረው፡-

- ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ፥ ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ፥ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው። እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን በሌሊት ያዘና ከጌታ ዘንድ በነቢይ። ልጄን ከግብፅ ጠራሁት የተባለው እንዲፈጸም ወደ ግብፅ ሄደ፥ ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ። ማቴ.፪፥፲፫-፲፭

## ስለ ምድራዊ ሥልጣን የሄሮድስ ጭካኔ።

ሰብዓ ሰገል ወደ እርሱ አለመምጣታቸውን ሄሮድስ ሲረዳ በቤተልሔም አውራጃ የሚገኙትን ሕፃናት አስገደላቸው። በዚህም አስቀድሞ በነቢያት ተነግሮ የነበረው ትንቢት በጨካኙ ሄሮድስ ተፈጸመ፡-

- የዋይታና የመራራ ልቅሶ ድምፅ በራማ ተሰማ፤ ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች፤ የሉምና ስለ ልጆችዋ መጽናናትን እንቢ አለች። ኤር. ፴፩፥፲፭

የእናት ጡት ያልጠገቡ፣ ንግግር የማያውቁትንና ገና በእናታቸው እቅፍ ያሉትን ሕፃናትን ሄሮድስ በግፍ አስጨረሳቸው። እንደ እግዚአብሔር መሆን ፈልጎ ያልተሳካለት እና ያለግብሩ አምላክነትን የከጀለው ሰይጣን ዲያብሎስ ከክብሩ እንደተዋረደ ባወቀ ጊዜ አዳምንና ሔዋንን አሳስቶ ከገነት እንዳስወጣቸው ሁሉ አሁንም በሄሮድስ ላይ አድሮ ሕፃናቱን በሙሉ አስጨረሰ። ሄሮድስ ከዓመተ ፍዳ እንዲወጣና ነፃነትን ገንዘብ እንዲያደርግ ወደ ምድር የመጣውን ኢየሱስ ክርስቶስን የምድር ሥልጣን ተጋሪው አድርጎት ለከንቱ ሥልጣን ሕፃናቱን እንዳስጨረሰ ሁሉ ዛሬም ምድራችን ለከንቱ ዝና ብቻ በመቆም በቤተ ክርስቲያን ሰላም እንዳይመጣ በማስደረግ ሕፃናት ነገ የእውነተኛይቱ ሃይማኖት ተረካቢ እንዳይሆኑ የሚያደርጉ ብዙ ሰዎችን አፍርታላች። የሄሮድስን ጭካኔ ገንዘብ ከማድረግ ይልቅ በክርስቶስ ያገኘነውን ሰላም ተጠቅመን ሕዝባችንን ከችግር ለማውጣት የየበኩላችንን ጥረት ማድረግ ይጠብቅብናል።

## የጌታችን ልደት የእኩልነት ቀን ነው።

ጌታችን ሲወለድ ሀብት ያላቸው ሰብዓ ሰገል፣ በድህነት ያሉ እረኞች፣ በሰማይ ያሉ መላእክት፣ በምድር ያሉ እንስሳት ተገኝተዋል። ዛሬም የጌታችንን መወለድ ሰምተው የሚደሰቱ እልፍ አዕላፍ ሰዎች በምድር ላይ አሉ። በአንፃሩም እንደ ሄሮድስ ዓይነቶች ከክብር ይልቅ ውርደትን፣ ከሰላም ይልቅ ሁከትን፣ ከማመን ይልቅ አለማመንን የመረጡ ብዙዎች አሉ። የተወለደው የሰላም አምላክ ሁላችንን የሚጠብቅ እረኛችን ነውና ከዚህ በረት ያልሆኑ ነገር ግን ወደዚህ በረት መግባት የሚገባቸው ብዙ በጎች አሉኝ ብሎ እንደተናገረው የአምላካችንን ፍቅር ቀምሰው ይረኩ ዘንድ እግዚአብሔር በተለየ ጥበቡ ወደ በረቱ ይመልሳቸው። የጌታችን መወለድ የእኩልነት ቀን መሆኑን ካመንን እኛ ፍጥረቶቹ ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ብለው ሰውና መላእክት እንዳመሰገኑት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ በማለት ልናመሰግነው ይገባናል። አምላክ ሰው ሰው አምላክ የሆነበት ይኽ ታላቅ ቀን ተዋሕዶነትን መሥርቶልናል። በልደቱ ሰላምን፣ አንድነትን፣ ክብርን፣ ፍቅርን፣ ትሕትናን፣ ውሕደትን ገንዘብ አድርገናል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!

አብርሃም ሰሎሞን።
Abraham Solomon
January 6/2011